# 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት
## እና የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ምረቃ

ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም

(November 22, 2014)

Time 9:00 am. - 6:00 pm.

ሰዓት ከጧቱ ፫ - ምሽቱ ፲፪ ሰዓት



“ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው።”

(መክብብ 3፥11)

Event location: Kena Temple

9001 Arlington Blvd

Fairfax, VA 22031

# “ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው።”
# (መክብብ 3፥11)

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን  እምነት ተከታዮች በሙሉ፤ በሕጋዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ላለፉት ሀያ ሁለት ዓመታት በስደት ለምትገኘው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ዕድገት፡ መስፋፋትና ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሰላም፤ አንድነትና ፍቅር ቅድሚያ በመስጠት ለትውልድ የሚተላለፉ  በርካታ ቋሚ ሥራዎችን ለመሥራት የቻለው በልዑል እግዚአብሔር ቸርነትና በምእመናን ብርቱ ድጋፍ  መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው።

ስለሆነም “ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም” (ማቴ. 8፥20) ተብሎ እንደተጻፈ ለቅዱስነታቸውና ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ማዕከል በመሆን የሚያገለግልና በየዕለቱ የሚሠሩ ሥራዎች የሚከናወኑበት ዋና ጽ/ቤት ሳይኖር እንዲሁ ሁሉም በአርለብት ቤተ ክርስቲያንም ሆነሌላ ቦታ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዕድገትና መስፋፋት ተቀዳሚ ዓላማ በማድረግ ላለፉት  በርካታ  ዓመታት መጠነ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል ስለሆነም ታላቁ ነቢይ ሰሎሞን “ቦ ጊዜ ለኵሉ፤ ለሁሉም ጊዜ አለው” (መክ. 3፥1-8) በማለት እንደተናገረው እነሆ ጊዜው ሲደርስ በስደት ዓለም ላለችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዋና ማዕከል የሚሆን የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የአሜሪካ ዋና ከተማ በሆነው በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የተገዛ መሆኑን በመላው ዓለም ለሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን  በታላቅ ደስታ እንገልጻለን።

በዚህም መሠረት ቅዱስነታቸው ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን ማዕረግ የበቁበትን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ ቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ የገዛውን አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ለማስመረቅ  በዝግጅት ላይ ይገኛል። ስለዚህ የቅዱስነታቸው 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት መታሰቢያና የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ፕሮግራም ህዳር 13  ቀን 2007 ዓ.ም (November 22, 2014) እንዲሆን በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ስብሰባ የተወሰነ መሆኑን በመላው ዓለም ላይ ለምትገኙ ኦርቶዶክሳውያን ወገኖቻችን በሙሉ በደስታ እየገለጽን በዚህ ታሪካዊና ታላቅ በአል ላይ በመገኘት የደስታችን ተካፋይ እንድትሆኑ  በአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ
አሜሪካ
የቦታው አደራሻ:

Event location: Kena Temple
9001 Arlington Blvd
Fairfax, VA 22031